በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ሚያዝያ 16 ቀን 2012
አዲስ አበባ

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ዜና መግለጫ**

የሚኒስትሮች ም/ቤት ሚያዚያ 16 ቀን 2012 ዓ/ም ባካሄደው 19ኛ አስቸኳይ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በኮሮና ቫይረስ ምክንያት በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ ያጋጠመውን አደጋ ለመቀነስ መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች የቀረበ የውሳኔ ሃሳብ ላይ ነው፡፡

በኮሮና ቫይረስ ምክንያት በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ ያጋጠመው አደጋ የአብዛኛውን የኅብረተሰብ ክፍል ኑሮ የሚጎዳ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት መንግስት ዘርፈ ብዙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፎችን እያደረገ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡ የዚህ ድጋፍ አካል የሆነውን የኢኮኖሚ ማነቃቂያ በማድረግ፣ ወረርሽኙ በኅብረተሰቡ ጤና ላይ የሚያደርሰውን አደጋ ለመከላከል የሚወስዳቸው እርምጃዎች ውጤታማ እንዲሆኑ፣ በወረርሽኙ  የተጐዱት የንግድ ሥራዎች እንዲሁም በወጪ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ድርጅቶች የከፋ ችግር ውስጥ እንዳይወድቁ፣ በተለያዩ መስኮች ተቀጥረው በሥራ ላይ ያሉ ሠራተኞች ከሥራ እንዳይሰናበቱ የድጋፍ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለማድረግ የገንዘብ ሚኒስቴር የውሳኔ ሀሳብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ም/ቤቱ በቀረበው የውሳኔ  ሀሳብ ላይ ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የኮሮና ቫይረስ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመከላከል መንግሥት ለሚያደርገው ጥረት የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉ ዜጎች እንዲበረታቱ በጎ አድራጊዎች ለመንግሥት የሚያደርጉት የገንዘብ ድጋፍ ግብር ከሚከፈልበት የ2012 ገቢ  ለግብር ክፍያ ላይ ከ20 በመቶ ያልበለጠ ተቀናሽ ማድረግን፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮች ታክስ የሚያስታውቁበት እና የሚከፍሉበት ጊዜ በአንድ ወር እንዲራዘም ማድረግን፣ የንግድ ድርጅቶች በስራ ላይ በቆዩባቸው ጊዜያት ያጋጠማቸው ኪሣራ ማሸጋገርን፣  በሥራ መቀዝቀዝ ምክንያት የጡረታ መዋጮውን ለመክፈል የተቸገሩ አሠሪዎች የሚቀጥሉትን ሦስት ወራት የጡረታ መዋጮ ሂሳብ ከሚጠበቅበት ከሐምሌ 1/2012 ጀምሮ እንዲከፍሉ የክፍያ ሽግሽግ ማድረግን በተመለከተ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012ን ማስፈፀሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ላይ የተወያየ ሲሆን ደንቡም በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

በመጨረሻም ምክር ቤቱ የተወያየው በገንዘብ ሚኒስቴር የቀረቡት የተለያዩ የብድር ስምምነቶች እና የማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ነው፡ ፡ ብድሮቹ ከጃፓን ዓለም ዓቀፍ የትብብር ኤጀንሲ ጋር የተፈረመውን ለጅማ-ጭዳ እና ሶዶ-ሳውላ የመንገድ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ፤ ከጣሊያን መንግስት ጋር የተፈረመውን የጤና ዘርፍ ዘላቂ የልማት ግቦች ፕሮግራም ማስፈጸሚያ፤ ከጣሊያን መንግስት ጋር የተፈረመውን የቴክኒክና ሞያ ስልጠና ክህሎት ማሻሻያ እና የስራ ፈጠራ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ፤ ከኮሪያ ኢምፖርት ኤክስፖርት ባንክ ጋር የተፈረመውን የአዲስ አበባ ከተማ ፈጣን አውቶብስ መስመር ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ፤ ከኮሪያ ኢምፖርት ኤክስፖርት ባንክ ጋር የተፈረመውን ለመሬት መረጃ አስተዳደር ስርዓት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ እንዲሁም ከተባበሩት አረብ ኢሚሬትስ የከሊፋ ፈንድ ለድርጅት ልማት ጋር ለአነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች የብድር አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውሉ ብድሮች ላይ ሲሆን ብድሮቹ ከሀገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣሙ፣ በረዥም ጊዜ የሚከፈሉ፣ ከ1% በታች ወለድ የሚከፈልባቸው እና ረዘም ያለ የእፎይታ ጊዜ ያላቸው መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት የብድር ስምምነቶቹ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ም/ቤቱ ወስኗል፡፡